# ትንቢተ ዳንኤል

## ሀ . የመጽሐፉ ፀሐፊ ዳንኤል

- የስሙ ትርጓሜ “ *እግዚአብሔር ዳኛዬ ነው !* ” ማለት ነው :
- ዳንኤል የኖረበት ዘመን ከ 680 - 534 ዓመተ ዓለም ድረስ ነበር :
- ነቢዩ ሕዝቅኤል የዳንኤል ወዳጅ ከመሆኑም ሌላ ሁለት ጊዜ በመጽሐፉ ውስጥ ጠቅሶታል

(ሕዝቅኤል ምዕራፍ ÷ 14 : 14 ፤ 28 : 3)
- እግዚአብሔር ራሱም በምዕ. 10 : 18-19 ላይ “ ***እጅግ የተወድህ ሰው ሆይ አትፍራ ፤ ሰ ላም ላን ተ ይሁን ፤ በርታ ፅና*** ” ይለዋል :
- መላዕክትም ስለዳንኤል የነበራቸው ምስክርነት በጣም የሚያደንቅ ነው: ገብርኤል በምዕ. 9 : 20 - 23 ላይ “ ***... አንተ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትዕዛዝ ወጥቷል እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ ...*** ” ሲለው እንመለከታለን ። በሌላ በኩል ደግሞ ለዳንኤል የመ ጣ ውን አምላካዊ መልስ በምድር ላይ እንዳይፈጸም በአየር ላይ ሲቋቋም የ ነበረው የሰይጣንን አሠ ራር መልአኩ ሚካኤል ሲዋጋው እንመለከታለን ። (ምዕ. 10 : 1 0 - 14)-ሰማያትና በጊዜው የነ በሩ ነቢ ያት ብቻ ሳይሆኑ የአህዛብ ነገሥታትም ስለዳንኤ ል ትልቅ ምስክነት ነበራቸው ። በአጠ ቃላይ በምዕ 1 : 3 - 4 ፤ 1 : 19 - 20 እናገኛለን ። በተጨማሪም ናቡከደነፆር ( 2 : 47 ) ፤ ብልጣሶር ( 5 : 29 ) ፤ ዳርዮስ ( 6 : 20 ፤ 26 ) የተናገሯቸው ሐሳቦች ማየት እንችላለን ።
- ጌታ ኢየሱስም ትንቢቱን አረጋግጦለታል ። በማቴ. 24 :15 ላይ “***እንግዲህ በነቢዩ በዳን ኤል የተ ባ ለውን የጥፋትን ርኩስት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል ፡...*** ” ይላል ።
- የዕብራውያን መጽሐፍ የፃፈውም ዳንኤል የእምነት ሰው እንደ ነበረ በምዕ. 11:34 ላይ ገ ልጾታል
- የዳንኤል ሕይወት ከዮሴፍ ሕይወት የሚመሳሰልበት ብዙ ነገሮች አሉ ÷

- ሁለቱም በወጣትነታቸው ጊዜ ነው የተማረኩት:
- ሁለቱም ያለፍትህ ነው የተሰደዱት :
- የሁለቱም ችግር ግን እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸው ክብር መሸጋገሪያ ድንጋይ ሆ ኖላቸውእንመለከታለን :
- እግዚአብሔር ሁለቱን ለማክበር የተጠቀመበት መንገድ በተረጎሙት ሕልም ምክንያ ት ነው
- ሁለቱም የኖሩበት ትውልድ በኃጢያት የተበከለ ቢሆንም የኖሩት ሕይወት ግን ያለነ ቀፋ ነበር:
- በመጨረሻም ሁለቱም የሞቱት በባዕድ ምድር ነው :

## ለ. የዳንኤል የሕይወት ታሪክ ÷

- ዳንኤል ያደገው በንጉሥ ኢዮስያስ ምክንያት በተነሳው መንፈሳዊ መነቃቃት መሀል ነው ፡ ይህም ሁኔታ እግዚአብሔር ወደፊት በዳንኤል ሕይወት ውስጥ በተለያዩ ነገሥታት መካከል ሊሠራው ላሰ በው ነገር ትልቅ ድርሻ ነበረው ፡ ( 2ነገ. 22 – 23 ፤ 25 )
- ስለወላጆቹ ምንም የተጠቀሰ ነገር ባይኖርም ከመሳፍንት ዘር እንደነበረ ግን ተጠቅሷል (ዳን.1፡4)
- የይሁዳ ሕዝብ የተማረከው በሶስት የተለያዩ ጊዜያት ነበር፡ ዳንኤልና ሶስቱ ወዳጆቹ ደግሞ የተማረኩት በመጀመሪያው የምርኮ ጊዜ ነበር ፥

1. የመጀመሪያው ምርኮ በ2ነገ. 24 ፡ 1 – 4 እንደምንመለከተው በንጉሡ ኢዮአቄም ጊዜ ነበር ጊዜው በ605/4 ዓ. ዓ ነበር ፡ በዚህ ምርኮ የተማረኩት ዳንኤልና ሶስቱ ወዳጆቹ ሌሎቹም ንጉሳውያን ቤተሰብ ናቸው፡

2. ሁለተኛው ምርኮ ፡ በ2ነገ. 24 ፡ 8 – 17 ላይ እንደምናየው በ597 ዓ. ዓ. እስራኤል በናቡከደነፆር ላይ ስላመፁ ሁለተኛው ምርኮ በዚያው ዓመት ተፈጸመ ፡ 10 000 የሰለጠኑ አናጢዎች ጥበበኞች አለቆች ፅኑአን ኃያላንም ተማረኩ ፡ የቤተመቅደሱም ዕቃ ሁሉ ተሰባበረ

3. ሶስተኛው ምርኮ በ2ነገ. 24 ፡ 18 – 25 ፤ 22 ድረስ እንደምንመለከተው በንጉሥ ሴዴቅያስ ዘመን በ 587/6 ዓ.ዓ. ነበር ፡ የተካሄደው በዚህ ጊዜ የኢየሩሳሌም ቅጥር ሁሉ ተሰባበረ ፡ ቤተመቅደሱም በእሳት ተቃጠለ፡

* – በመጽሐፉ መደምደሚያ አካባቢ የዘጠና ዓመት ሽማግሌ ቢሆንም እግዚአብሔር ለሚሰጠው ራዕይና መገለጥ ክፍት ከመሆኑም በላይ ፡ እግዚአብሔር የታሪክን ሂደት ሲቀርፅም ምክንያት ሆኖ ለመገኘት የቀረጠ ልብ ነበረው ፡

*

- በመጨረሻም አይሁድ ከተማረኩበት ከባቢሎን ምድር ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለከቱም ሆነ ፥ ባቢሎንም ስትወድቅ በሕይወቱ ዘመን አይቷል ፡

## ሐ . የዳንኤል መጽሐፍ ልዩ መጽሐፍ ነው ፡

1. ዳንኤል ነቢይ እንደሆነ የሚገልጽ ምንም አገላላጽ አልተጠቀመም፡

2. በሌላ በኩል ደግሞ እንደሌሎቹ የታሪክ መጻሕፍትም የታሪክ መጽሐፍ ብቻ አይደለም ፥ የሚመጣውም ዓለም ታሪክ ነው ፡

3. መጽሐፉ ከአንድ ዕውነት ተነስቶ ወደ ታሪኮች ሁሉ መደምደሚያ (ጣሪያ) የሚወስደን ስለሆነ ሊመጣ ያለውንም የእግዚአብሔር መንግሥት ክብር በግልጥ ያሳያል ፡

4. እንደመጀመሪያዎቹ የዘፍጥረት ምዕራፎች ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው መጽሐፍ ነው ፡

## መ. መጽሐፉ በሁለት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል ፡

**ምዕራፍ** 1 – 6 ፥ ***ታሪካዊ ይዘት ፡***

**ምዕራፍ** 7 – 12 ፥ ***ትንቢታዊ መገለጥ ያለው ይዘት ፡***

| |
|---|
| * ምዕራፎቹን በቅደም ተከተል እናስቀምጥ ብንል እንደሚከተለው ይሆናሉ ፥<br>1 – 4 , 7 , 8 , 5 , 9 , 6 , 10 – 12 . |

## ሠ. የመጽሐፉ ጭብጥ ሐሳብ (መሪ ሐሳብ )

" ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የእግዚአብሔር ችሎት "     **ምዕራፍ** 2 ፡ 28